# ★ ዴሞክራሲያ ★

* የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ዴሞክራሲያዊ) ልሳን*

**ቅጽ** 41 **ቁ.** 2 **የካቲት** 2007


## የካቲትና ዓድዋ፤ የወርና የሥፍራ ጥልቅ ትርጉም

የየካቲት 1966 ዓ.ም. ሕዝባዊ እንቅስቃሴንና የ1888 ዓ.ም. የዓድዋ ጦርነትና ድልን ብዙ የሚያገናኟቸው ነገሮችና የሚያስተሳስሯቸው ክሮች አሉ። የካቲት አዝሎት የነበረው ሕዝባዊ ተስፋ መጠነ ሰፊ ነበር። በረሃብ ዘወትር የሚጠቃው ሕዝባችን በቀን ሦስት ጊዜ የሚመገበው የተመጣጠነ ምግብ እንዲያገኝ፣ ጤና ጥበቃው እንዲሟላ፣ ትምህርት ያልደረሰው ወገን ትምህርት እንዲያገኝ፣ የነበረው የትምህርት ሥርዓትም የተሟላና ከምርትና ከዕድገት ጋር የተያያዘ እንዲሆን፣ ንጹህ ውሃ፣ እንዲሁም የኤሌክትሪክ መብራት ተጠቃሚ እንዲሆን፣ በረንዳ አዳሪነት ቀርቶ ለአንገቱ ማስገቢያ በቂ መጠለያ እንዲያገኝ፣ ችሎታ ያለው በችሎታው፣ ችሎታ የሌለው በሥልጠና፣ ቢወድ በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች፣ ቢሻው ደግሞ በግል መስኩና የራሱንም ሥራ ጭምር የሚከፍትበትና የሚተዳደርበት ሥርዓት እንዲመሠረት፤ ሴቶች ወገኖቻችን ነፍስና ሥጋን ለማቆም በልቶ ለማደር ብቻ ሰብዓዊነትን ከሚያቆሽሽ ሴተኛ አዳሪነት ኑሮ እንዲወጡና ራሳቸውን ረድተው አገራቸውንም በሚረዱበት መስክ የሚሳተፉበት ሥራ ላይ እንዲሰማሩ፣ ወሮበላነትና ወንጀለኝነት በአስተምህሮና በአዎንታዊ ማረሚያ መንገዶች የሚቀንሱበት ተስፋና ምኞትን የካቲት ተሸክሞ ነበር።

መጠነ ሰፊው ተስፋ ከላይ በተዘረዘሩት ብቻም አያበቃም። ጉቦኝነትና የመንግሥትና የሕዝብ ሃብት መዝረፍ እንዲቀር፣ በገጠሩ ሕዝብ መካከል ከተሞች ከዘመናዊ ስጦታዎቻቸው ጋር (መብራት፣ ጥርጊያ ጎዳና፣ የሕዝብ ማመላሻዎች፣ የጤና፣ የትምህርትና ሌሎች ማኅበራዊ ተቋማት) የሚስፋፉበትና በእርሻ የሚተዳደረው ሕዝብ እስካሁን ድረስ ካለበት 80 በመቶ ወርዶ የእርሻ ኢኮኖሚ ወደ እንዱስትሪ ኢኮኖሚ የሚለወጥበት፣ በገጠርና በከተማ ኪነጥበብ፣ ሥነ-ጽሁፍ፣ ተውኔት፣ ስዕል፤ በሰፊው ሕዝብ ዘልቀው የሚደርሱበት ሥርዓት የመፍጠር ተስፋ ነበር።

እነዚህ ሁሉ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተስፋዎች ተፈጻሚነት እንዲኖራቸው ደግሞ የካቲት ፖለቲካዊ ተስፋም አንግቦ ነበር። ማን እቅዱን ያወጣል? ማን እቅዱን ይተቻል? ማን እቅዱን ያስፈጽማል? ማንስ ተፈጻሚነቱን ይከታተላል? ለሚሉትና ለመሳሰሉት ጥያቄዎች ሁሉ የካቲት ተስፋዊ መልስ ሰጥቶ ነበር። ሥልጣን የሕዝብ እንዲሆን፣ አገሪቱ በሕዝብ በተመረጡ ዜጎች እንድትተዳደርና ሕዝባዊ መንግሥት እንዲመሠረት፣ ዳኝነት ፍትሃዊ በሆነና ነፃ በሆነ መልኩ እንዲሰፋፋ፣ ሰብዓዊና ፖለቲካዊ መብቶች፤ ማለትም በፖለቲካ ድርጅትም ሆነ በሠራተኛ ማኅበር የመደራጀት መብት እንዲከበር፣ በነፃነት የመጻፍ፣ የመወያየት...ወዘተ መብቶች ያለገደብ እንዲከበሩ የካቲት ተስፋውን ሰንቆ ነበር። ይህም ማለት የሕዝብ እንደራሴዎች ያወጡትን እቅድ ጠቃሚነት፤ ብሎም ተፈጻሚነት የሚከታተልና ለሕዝብ በየጊዜው የእድገቱን አካሄድ በሃቅ የሚያስታውቅ ነፃ የመገናኛ ብዙሃን እንዲኖር የካቲት ተመኝቶ ነበር።

በከተሞች ወጣቶች ከትምህርት ሰዓታት ውጭ የሚዝናኑባቸው፣ ሰውነታቸውን የሚያፍታቱባቸውና የሚያጠነክሩባቸው፣ ዜጎች በአዘቦት ቀኖች የሚዝናኑባቸው መናፈሻ ቦታዎች፣ የኳስና የሩጫ ሜዳዎች፣ በእቅድ በስፋት የሚሠሩበትን፣ መንግሥታዊ የደህንነት ተቋሞች ማለትም ወታደሩ፣ ፖሊሱና ደህንነት ጥበቃው፣ ተልእኳቸው የሕዝብ ጋሻና ጠባቂ፣ የአገር ሉዓላዊነት አስከባሪ ዜጎች በሰላም መኖራቸውን ማረጋገጥና ህገ-መንግሥቱ መከበሩን አረጋጋጭ እንዲሆኑ የካቲት አልሞ ነበር። ይህ ብሩህ የሕዝብ ተስፋ እውን እንዲሆን ያ ትውልድ ክቡር የሆነውን ሕይወቱን አሳልፎ ሰጥቷል።

እነዚህንና ተጓዳኝ ተስፋዎችን ይዞ የዛሬ 40 ዓመት የተነሳው ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ምኞቱና ክንውኖቹ በሚዛን ላይ ሲታዩ ሁኔታው ምን ይመስላል? የሚለው ጥያቄ ተገቢ ነው። በተለይ የካቲት እነዚህን አስጎምጂ ተስፋዎች፤ ውድ አገራችን ኢትዮጵያን የምድር ገነት የሚያደርጉ ተምኔቶችን ተሸክሞ ሲያውጅና ሲውተረተር ለማየት ያልበቁ፤ በወቅቱ ህፃናት ከነበሩት ጀምሮ ዛሬ ዕድሜያቸው 40ና ከዚያ በታች የሆኑ ከአገራችን የሕዝብ ቁጥር አንፃር ከግማሽ በላይ የሆኑት ወጣት ዜጎች ቃልና ግብር ዛሬ አራምባና ቆቦ ሲሆን በዓይናቸው እያዩ ቢገረሙ ተስፋውን ያኔ ለኖርነው አስገራሚ ሊሆን አይገባም።

ይህ ትውልድ ተስፋው ተፈጻሚ እንዳልሆነ በዓይኑ የሚያየው፣ በእጁ የሚዳሰሰው፣ በአፍንጫው የሚያሸተው ሃቅ ስለሆነ ባመዛኙ በአብዛኛው ስምምነት እንደሚኖር መገመት ይቻላል። አንዳንድ ልዩነት ሊኖር የሚችለው "ለምን ህልሙ እውነት አልሆነም?" በሚለው ትንተና ላይ ሊሆን ይችላል።

ዋናው ነገር ግን "እባብ ያየ በልጥ በረየ"ን ወደጎን ትቶ ዛሬም የ40 ዓመት ዕድሜ ያለውን የየካቲት ህልም፣ የየካቲት ምኞት፣ በአዲስ ትውልድ፣ በአዲስ መንፈስ፣ በአዲስ ተስፋ እንደገና አልሞ፤ አንድ ትውልድ ጀምሮ ያልፈጸመውን የዛሬው ትውልድ በራሱ መንገድ እንዲያልመውና ተፈጻሚ እንዲያደርገው ታሪክ ጥሪዋን ታቀርባለች። የህልሙ መሠረት ደግሞ ኢትዮጵያን ኢትዮጵያ የሚያሰኟት፣ ጎሳዎቿና ብሄረሰቦቿ ባንድ ድምፅ የዜግነት ፍቅራቸውንና አንድ ስንደቅ ዓላማቸውን እያውለበለቡ ነፃነታቸውን እንደ ዓይናቸው ብሌን የሚጠብቁት ኩሩ ዜጎቿ ናቸው። ለዚህ ጽኑነት ዋናው ዋቢ ደግሞ የ1888 የዓድዋ ጦርነትና ድል ነው።

ወደ 120 ዓመታት ለማስቆጠር የተቃረበው በጣሊያን ላይ የተገኘው ሃገራዊና ኢትዮጵያዊ ድል በሥነ-አእምሮአችንና በሥነ-ልቦናችን ላይ የፈጠረው ኩራትና የዜግነት ክብር ቀላል አይደለም። ተደጋግሞ እንደተባለው፤ ይህ ኩራት በእኛ ብቻ ሳይወሰን ለመላው ጥቁር ሕዝብና ፍትህን ወዳጁ ላደረገ የዓለም ዜጋ ሁሉ ኩራት ነበር። ሥፍራው ዓድዋ ኢትዮጵያ ውስጥ እንጂ ጣሊያን አገር አይደለም። ጣሊያን ዓድዋ ላይ ጦርነት የከፈተብን በአጥቂነት እንጂ በተከላካይነት አልነበረም። የመጣው የጦርነት ዝግጅት አድርጎ፤ ባህር ተሻግሮና አቋርጦ ነበር። ያካሄድነውና ያሸነፍነው ጦርነት ፍትሃዊና ያገራችንን ነፃነት ያስከበረ ነበር።

ልክ በየካቲት (ከዓድዋ ጦርነት 86 ዓመታት በኋላ) ምልዓተ ሕዝቡ በኢትዮጵያዊነቱ በጋራ ተስፋ ሰንቆ እንደተንቀሳቀሰ ሁሉ፤ ወደ ዓድዋ ጦርነት ሲዘመትም ምልዓተ ሕዝባችን፤ ከሰሜን እስከደቡብ፣ ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ የንጉሡን የአፄ ምኒልክንና የንግሥቲቱን እቴጌ ጣይቱን ትዕዛዝ በመቀበል፣ ስንቁን ሰንቆ የተመመበት፣ በጋራ የተዋደቀበትና በጋራም ያቸነፈበት ጦርነት ነበር። ኢትዮጵያዊ የካቲት፤ ኢትዮጵያዊ ዓድዋ። የካቲት የተስፋ ስንቅ፤ ዓድዋ ደረቅ ስንቅ።

በድላችን መኩራቱና መኩራራቱ ተገቢና አስፈላጊ ነው። የዓድዋ ድልም መዘከር ያለበት በዓል ነው። ሆኖም ዞር ብለን ደግሞ ከዚያ ወዲህ የነበረብንን ችግርና ዛሬም ያለንበትን ሁኔታ ማጤን ደግሞ፣ ወደፊት ለምንሄድበት አቅጣጫ አመላካች ስለሆነ ከኩራቱ ጎን ተግዳሮቶቹንም ማውሳት ተገቢ ነው።

ተግዳሮቶቹ ከፊሎቹን ሕዝባችን ድል ሲያደርጋቸው ሌሎቹ ደግሞ ዛሬም ይፈታተኑናል። ከዓድዋ ድል ወዲህ ዋና ዋናዎቹ ተግዳሮቶች፣ እንደገና ለሁለተኛ ጊዜ ጣሊያን ከዓድዋ ድል 40 ዓመት በኋላ ባህር ተሻግሮ መጥቶ፣ በዓለም ማኀበር በተከለከለ የመርዝ ጢስ

ሕዝባችንና ከብቶቻችንን፣ ዛፎቻችንን ሁሉ ያወደመበት አስከፊ ጦርነት ቅድሚያውን ይይዛል። በአርበኞቻችን ትግል ነፃነታችንን ለማስመለስ ብንችልም፤ አገራችን የሕዝቦቿን የኑሮ ደረጃ በማሳደግ ደረጃ አመርቂ ጉዞ ባለማሳየቷ፣ በተለይ በ1966 ዓ.ም. አካባቢ በወሎና በትግራይ ክፍለሃገሮች የታየው ረሃብ፣ የፈጀው ሕዝብና እንስሳት፣ ከፍተኛ የአእምሮ ጠባሳ ትቶብን አልፏል። ለየካቲት እንቅስቃሴ መነሳሳትም ከምክንያቶቹ ዋነኛው ሆኗል። የካቲትን ተከትሎ በደርግ መንግሥት ወቅት የተካሄደው ቀይ ሽብር ደግሞ ሌላው አስከፊ ቀውስ ነበር። በአገራችን ታሪክ ታይቶም ተሰምቶም በማይታወቅ ደረጃ ወጣትነት ብቻ እንደ ወንጀል ተቆጥሮ፤ "ነፃ እርምጃ" በተባለ አረመኔያዊ ጥቃት በአሥር ሺዎች የሚቆጠሩ ወጣቶች ለሞት፤ ለእሥርና ለስደት ተዳርገዋል። ይህ ነውረኛ ሽብር በዚህ ብቻም አላበቃም። እናቶችና አባቶች የተገደሉባቸውን ልጆች አስክሬን ለማግኘትና በእምነታቸው ሥርዓት ለመቅበር ሲሞክሩ "ለባከነው ጥይት" ወጭ እንዲከፍሉ ተገደዋል። ሟች ወጣቶች መንገድ ላይ ተሰጥተው በአውሬ ተበልተዋል፤ ወላጆች ለሟች ልጆቻቸው ሃዘን እንዳይቀመጡና እንዳያለቅሱ ተከልክለዋል።

ከዓድዋ ድል በኋላ ዋነኛው ተግዳሮት ሕዝባችን የወደደውን መንግሥት በምርጫ ለማቆም ያለመቻሉ ህጸጽ ነው። ንጉሥ ምኒልክን የተኩት አፄ ኃይለሥላሴ 43 ዓመት ሲነግሱ አገራችን ውስጥ ተፎካካሪና ህገ-መንግሥታዊ ፓርቲዎች እንዲመሠረቱ ተነሳሽነት አልወሰዱም። እሳቸውን የተካው ደርግም 17 ዓመት ሙሉ ስሙን ሲለዋውጥና አገር ሲያተራምስ ቆይቶ ከአንድ ፓርቲ አምባገነንቱ ጋር አልፏል።

ከሁሉም በከፋው መልኩ ዓድዋንና የቆመበትን ዓላማ የተፈታተነው የዛሬው ዘረኛ ሥርዓት ነው። ኢትዮጵያዊነትን በማንቋሸሽ፤ የዓድዋን ድል አራክሷል። በእስካሁን በአንፃራዊ ሰላም በሚኖሩ ኢትዮጵያውያን መካከል ሆን ብሎ የጦርነትና የማፈራረቅ ፖሊሲ እየተከተለ ለብዙ ሺህ ዜጎች መሞት፤ ከተወለዱበት ሥፍራ መፈናቀልና ለሀገር ውስጥ ስደት ተጠያቂ ነው። በደቡብ ኢትዮጵያ በጉጂና በቦረና ዜጎች መካከል፤ በጋምቤላ በአኙዋኮችና በኑዌሮች መካከል፤ ዛሬ በጎንደር አካባቢ በቅማንቶችና በአማሮች መካከል ጥርጣሬና መፈራረቅ በመፍጠር፤ ኢትዮጵያዊነትን ያለማቋረጥ በሥልጣን ላይ በቆየባቸው 24 ዓመታት ሸርሽሯል። አማሮች ከተወለዱበት፣ ቤተሰብና ንብረት ካፈሩበት ከደቡብ ኢትዮጵያ፣ ከቤኒሻንጉልና ከሌሎችም ቦታዎች ያላግባብ በማስገደድ እንዲባረሩ ተደርጓል።

ዓድዋንና ድላችንን አሁንም በመፈታተን ህወሓት/ኢህአዴግ የዓድዋ ጀግኖች ደማቸውን ያፈሰሱበትንና አጥንታቸውን የከሰከሱበትን ዓላማ አዋርዶ ለም መሬታችንን ለውጭ

ከበርቴዎች በርካሽ ይቸበችባል። እነዚህም ዲታዎች በርካሽ በገዙት መሬት ላይ ያመረቱትን ሰብል ወደ ሀገራቸው ይጭናሉ፤ ወይም በውድ ዋጋ እየሸጡ ይከብራሉ።

ዓድዋን፤ የካቲትን፤ ሥፍራን፣ ወርን፣ ዓላማን በማዋረድ ተፎካካሪ ያላገኘው ህወሓት/ኢህአዴግ፤ አገራችንን ወደብ አልባ በማድረግ ከ90 ሚሊዮን ሕዝብ በላይ የውጭ ባህር መተንፈሻ እንዳይኖረው አድርጎ አገሪቱን ለጠላት ጥቃት በማጋለጥና ለወደብ አገልግሎት የአገሪቱን አንጡራ ሃብት ለጂቡቲና ለሌሎች በማፍሰስ የሚገኝ ከሃዲ ቡድን ነው።

የየካቲት የተስፋ ስንቅና የዓድዋ ደረቅ ስንቅ ወንዝ እንዲያሻግሩ ከተፈለገ የዛሬው ትውልድ ከፍተኛ ሃላፊነት አለበት። የዜግነት ግዴታውን ጠንቅቆ መረዳት አለበት። ሰብዓዊ መብቱንና ፖለቲካዊ መብቱን የነጠቀውን አገዛዝ ለመፋለም መዘጋጀት አለበት። የዜግነት መብታቸውን ተጠቅመው የጻፉትን፤ ያሳወቁንን፤ ወጣቶች "አሸባሪዎች" እያለ ከዓመት ዓመት ቁጥራቸው የጨመረ የፖለቲካ እስረኞችን ለማስፈራሪያና "እኔን ያየህ ተቀጣ" በሚል የሥነ-ልቦና ጦርነት በወጣቱ ላይ እንደከፈተ ሊገነዘቡ ይገባል።

የካቲትና ዓድዋ ያስተማሩን ያለትግል መብት እንደማይገኝ እንደሆነ ነው። ለዚያውም፤ ዓድዋ ላይ ነው እንጂ ቀጥተኛ ድል የተገኘው፤ የካቲትማ ያ ሁሉ መስዋዕትነት ተከፍሎም ተስፋዎቹ ዛሬም ተስፋ ብቻ ናቸው። ይህ ግን ትግል በጥበብና በዘዴ መመራት እንዳለበት ብቻ ነው የሚያስተምረን። የካቲት ላይ የጎደሉትንና ተስፋው ወደ ድል እንዳይለወጥ የገረገሩትን ህጸጾች መዝዞ አውጥቶ ፍቱን መድሃኒታቸውን በቦታው ማስቀመጥ የወቅቱ ግዳጅ ነው።

አንደኛውና ዋነኛው ጉድለት የታጋዮች ኅብረት አለመኖር ነው። ዛሬም ይህ ተደጋግሞ እየታየ ነው። ከየካቲቱ ድክመት በፍጥነት ተምሮ የፖለቲካ ድርጅቶች፤ ሲቪክ ድርጅቶችና ሌሎች ማኅበሮች ሁሉ አገር ቤትም፤ ውጭም የሚገኙ ወደ አንድ እንዲጠቃለሉና ትግላቸው አካል ገዝቶና ገዝፎ የየካቲትን ተስፋ ተፈጻሚ እንዲያደርግ ወጣቱ ትውልድ ከፍተኛና መሪ ሚና ሊጫወት ይገባል።

ኩሩውና ይሉኝታ ያለው ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ በዓለም ሕዝብ ፊት ከሚገባው የኑሮና የባህል ደረጃ ላይ እንዲደርስ የነበረውን ተስፋ በደካማው ጀርባ የተሸከመው የካቲት 1966 ብዙ ሳይጓዝ በደርግ፣ በህወሓትና በኢትዮጵያ ጠላቶች ምት ሽብረክ ብሎ፣ ተስፋው እንዲያብብና ፍሬ እንዲያፈራ ማነው የሚታደገኝ?" በማለት እጆቹን ዘርግቶ "የዜጋ ያለህ፤

የወጣት ያለህ፤ እያለ ትኩስ ዜጋን ነጋ ጠባ ይማለዳል። አዎንታዊ መልሱ በወጣቱ እንደበትና ምግባር በቅርብ የሚታይ እንደሚሆን መተማመን ይቻላል።

የዓድዋ ድል አንጸባራቂ ነው!
የየካቲት የተስፋ መፈክሮች ይፈጸማሉ!